
# የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ያስተናገደው፤ የመደመር ፖለቲካ በባህርዳር

**Wednesday, 04 July 2018 13:08**

- በ ጋዜጣው ሪፖርተር



ሰኔ 24 ቀን 2010 ዓ.ም ባሕርዳር ከተማ የ"መደመር ቀን" በሚል መሪ ቃል በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ የከተማውና የአካባቢው ሕዝቦች በአንድ ላይ ተሰባስበው በተለያዩ ዝግጅቶች አክበርዋል። አምስት መቶ ሜትር ርዝመት በስድስት ሜትር ስፋት አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንድራ ይዘው በውጣት ዝግጅቱን አድመቀውታል።

የሰለፉ መሰረታዊ ዓላማ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ የ"መደመር" ፖለቲካዊ መርህን ለመደገፍና፤ ለመደመር ያለመ መሆኑን ከአዘጋጆቹ ተደምጧል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአካል በስብሰባው ላይ ባይገኙም "ለባሕርዳር ከተማ እና አካባቢው ነዋሪዎች የከበረ ሰላምታ እና መልካም የለውጥ ምኞታቸውን" በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ለታዳሚው አስተላልፈዋል።

በባሕርዳር ስታዲየም ዝግጅት ላይ በርካታ ሰዎች ተጋብዘው ንግግር አድርገዋል። ንግግር ካደረጉት መካከከል አቶ ደመቀ መኮንን፣ አቶ ገዱ አዳርጋቸው፣ ብርጋዴን ጀነራል አሳምነው ፅጌ፣ ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ እና አቶ ሽባባው የእኔአባት ይገኙበታል። በቀረቡት ንግግሮች ላይ ተንተርሰን ፖለቲካዊ ትንታኔዎች ከማቅርብ፤ የመረጥነው እንዳለ ማቅርብ ነው። ምክንያቱም ንግግር ካቀረቡት ሰዎች አውድ ውጪ፣ ትንታኔ ከማቅረብ ለመቆጠብ ነው።

በድጋፍ ሰልፉ ላይ ለየት ያለና ወደፊት ብዙ ሊያነጋግር የሚችል ሃሳብ የተሰነዘረው ከወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ ነው። ይኸውም፤ ወ/ሮ እማዋይሽ ለድጋፍ ሰልፈኛው ያቀረቡት ጥያቄ "የአብረን እንስራ ጥሪ ሲቀርብልን በተቀደደልን ቦይ ለመፍሰስ ነው ወይንስ የሽግግር መንግስት ለማቋቋም?" የሚል ነው። ይህ ሃሳብ ብዙ ጉዳዮች የታጨቁበት ብዙ ገጽ ወሬ መልዕክት ያለው መሆኑን ብንገነዘብም፤ እሳቸው ካሉት በላይ ብዙ ዕርቀት መሄድ አልፈለግንም።

ሆኖም ግን የድጋፍ ሰልፉ ገዢ ሃሳብ ይሆናሉ በማለት የብአዴን ሊቀመንበር የአቶ ደመቀ መኮንን እና የምክትል ሊቀመንበሩን የአቶ ገዱ አዳርጋቸውን ንግግሮች በተቻለ መጠን ሙሉውን አስፍረነዋል። በሊቀመናብርቱ ሊተላለፉ የተፈለጉትን መልዕክቶች፣ አንባቢዎቻችን በተረዳችሁበት አግባብ እንድትወስዱት ለእናንተው ተውነው። የአውዱን ፍቺ ነፃነት ለመጠበቅ በማሰብ ነው። መልካም ንባብ።



ም/ጠ/ሚ አቶ ደመቀ መኮንን
ባህርዳር ላይ ያስተላለፉት መልዕክት

# ም/ጠ/ሚ አቶ ደመቀ መኮንን

# ባህርዳር ላይ ያስተላለፉት መልዕክት

በቅድሚያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ . . . በአካል በዚህ ታሪካዊ ሰልፍ ላይ ባይታደሙም፤ በመንፈስ ግን አብረውን እንደሆኑ በመግለጽ ለባህርዳር ከተማ እና የአካባቢዋ ነዋሪዎች የከበረ ሰላምታ እና መልካም የለውጥ ምኞታቸውን በክብር አስተላልፈዋል።

እነሆ ዛሬ! እንደዚህ በደመቀ አብሮነት እና ባሸበረቀው ህዝባዊ ሰልፍ በመካከላችሁ ተገኝቼ ይሄን ንግግር ሳደርግ የተሰማኝ ልባዊ ደስታ እና የፈጠረብኝን ውስጣዊ ፍሰሃ ምንኛ ትልቅ እንደሆነ እኔ ብቻ ነኝ የማውቀው።

ይህ ታሪካዊ ቀን ቀጣዩን ጊዜ የተሻለ እና ክልላችንን እና ሀገራችንን ተመራጭና ተወዳጅ፣ የሰላምና የልማት ምድር ለማድረግ ብሩህ ዕለት የወገገበት ነው። ለዚህ ዕለት ዕውን መሆን በየፈርጁ የታገሉ፣ የደሙና የቆሰሉ፣ ከዚያም አልፎ ክቡር ሕይወታቸውን የሰው በዚህ አደባባይ ክብርና ሞገስ ለእነሱ ይሁን። እናመሰግናለን።

ባህርዳር የክልላችን መናገሻ ከተማ ብቻ ሳትሆን፤ በለሱ ቀንቷቸው ጎራ ያሉ የሃገራችን እና የሌሎች ዓለም ሰዎች በፍቅር የሚማረኩላት፤ ስለውበቷና ስለምቹነቷ ደጋግመው የሚመሰክሩላት፤ የሃገራችን ከተሞች ፈርጥ ነች።

ባህርዳር - ጣናን ተንተርሳ፣ ጊዮንን እንደመቀነቷ አገልድማ ታላላቅ ጥበቦችን በማህፀኗ ያቀፈች ድንቅ ሃብታችን ነች። አሁን. . .አሁን! በሃገር አቀፍ ደረጃ የዘመናዊነትና የብልፅግና ማሳያ ምልክት ከሆኑ ውብ ከተሞች መካከል አንዷ ባህርዳራችን ነች። እንኳን በዚች ውብ ከተማ በሚካሄደው ደማቅ ህዝባዊ ሰልፍ ላይ በጋራ ለመታደም አበቃችሁ፤ አበቃን።

ይህ ትዕይንት፣ የለውጥ ጥማት፣ የዴሞክራሲና የሠላም ፍላጐት ብቻ አይደለም። ኃይልም ነው። ጉልበትም ነው። ሁሉንም ዕውን የሚያደርግ አቅም ነው። ዛሬ እዚህ ፊት ለፊታችሁ ቆሜ በአይበገሬነትና በተስፋ የሚደልቀው ልባችን ዓለት ሲያንቀጠቅጥ፣ ድህነትን ሲንጥ ይሠማኛል። ለዓለም ሁሉም ይሰማል።

ይህ አስደማሚ የጥምረታችን ኃይል የትኛውንም መሰናክል ገርስሶ፣ እንቅፋቶችን ሁሉ አፍርሶ ድህነትና ኋላቀርነትን ታሪክ እንደሚያደርግ አልጠራጠርም። ይህ እንዳለላ ሙዳይ፣ እንደ ህብር ሙካሽ የተንቆጠቆጠ ውበታችን የኢትዮጵያዊነት ፈርጥ ሆንነ፤ ሕዝቦቿን በውበት ሠድረንና ደምረን ለሀገራችን ድምቀት እንደምንሆን ይሄው ያየን ሁሉ ይመሰክራል። አብረን ቆመን አንጀታችን እንደክራር፣ ልባችን እንደከበሮ ተዋህዶ እየፈጠረ ያለው ዜማ ልዩ ኅብረ ዝማሬ ነው። ለሁሉም የሚጥም፣ ሁሉም የሚሰማው፣ ሰሞቶ የሚያበቃው ብቻ ሳይሆን አብሮ የሚደመርበት የፍቅር ቅኝት ነው። ፍቅራችን ሁሉንም ያሸንፋል።

የዛሬው የምስጋናና የድጋፍ ትዕይንት እያደር በየፈርጁ የሚገለጥ የአደራ ጥራዝ የብርታት ስንቅ ነው። አደራው የሁሉም፤ አቅሙም የጋራ ነው። ይህን ለውጥ ከዳር ለማድረስ ስንበረታ እንደዛሬው ተመሰጋግነን፣ ስንሰንፍ ተወቃቅሰን፣ ተግሳፃችሁን ሰምተን ልንታረምና ልናገለግላችሁ ቃል የምንገባበት መድረክም ነው።

በዘመን ቅብብሎሽ አያቶቻችን እና አባቶቻችን . . . በአገር ፍቅር የነደደው ነፍስ፤ በነፃነት ጥማት የተሞላው መንፈስ፤ ለችግር የማይንበረከክ ነፃና ኩሩ ህዝብ፤ በፈተናዎች ፊት ፀንታ ሳትበገር የምትቆይ ሃገር አቆይተውናል።

ገና ከጥንቱ! አገርና ህዝብ ሲደፈር "ከራስ በላይ ንፋስ!" የሚል አስተሳሰብን አሸቀንጥረው "ከራስ በላይ ሃገር!" መኖሩን በታላቅ ጀግንነት ወድቀው፤ ተዋድቀው ክብሯን የጠበቀች እና ነፃነቷን ያስጠበቀች ሃገር በአደራ አውርሰውናል።

በቀደሙት የታፈረችውን ሃገር፤ በእኛ ደግሞ . . . የለውጥ ጉዟችን ፈተና ቢበዛውም ሃገራችን ከስኬት ማማ ላይ እንድትታይ በቁጭት እና በስስት ለውጥን በምኞት ሳይሆን በተግባር ለማምጣት የምንታትርበት ምዕራፍ ላይ እንገኛለን።

እነሆ ዛሬ! ያለማንም ቀስቃሽ እና ጎትጓች በገዛ ፍቃዳችን በዚህ ታላቅ ስቴዲየም የተገናኘነው በተጀመረው ሃገራዊ አዲስ የለውጥ ስሜት አጋርነታችንን ለመግለፅና ይኸው ለውጥ በክልላችን ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ባለቤትነታችንን ለማሳየት ነው።

ባለፉት ዓመታት በአገር ደረጃም ሆነ በክልላችን ለለውጥ መነሻ የሆኑ ስራዎች ተመዝግበዋል። ነገር ግን ከሚጠበቀው ለውጥ አኳያ የሰራነው ትንሽ፤ የወቃነው ደግሞ ዕፍኝ እንደማይሞላ እንገነዘባለን።

ዛሬ የሰጣችሁን ድጋፍ እና የለገሳችሁን ምስጋና የከረሙ ችግሮችን በሙሉ ጠራርገን ስላስወገድን እንዳልሆነ በሚገባ እንረዳለን። ዋናው ነገር ጅምር የለውጥ አያያዛችን "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል!" የሚል መነሻ መሆኑን አንዘነጋም።

ለውጡን በሚጠበቀው ከፍታ ለማስቀጠል በየደረጃው ያለን መሪዎች ካለፈው ጉድለታችን ተምረን ቃላችንን ለማደስና ህዝባችንን ለመካስ ከፊታችሁ ቆመናል። ንቅናቄው ጥቂቶች የሚዘውሩት፤ ብዙዎች የሚታዘቡት ሳይሆን ሁሉም በባለቤትነት ሊተውንበት የሚገባ ነው።

በዚህ መስተጋብር መሪዎች ስናጠፋ እየተቆነጠጥን፤ በጎ ስንሰራ እየተበረታታን እንድንቀጥል ዛሬ ብቻ ሳይሆን ሁሌም ከጎናችን ታስፈልጉናላችሁ።

ህዝቡ ባልተሸበበ አዕምሮ በነፃነትና በሃላፊነት መንፈስ ድጋፍና ተቃውሞውን የመግለፅ ባህሉ መጠናከር አለበት።

ህዝቡ እንደ ንስር ዓይን ችግሮችን ነቅሶ የሚያወጣበት እና እንደ ዶ/ር አዲስ አለማየሁ የተባ ብዕሩ ስንዴውን ከእንክርዳዱ የሚለይበት አቅሙን ከመቼውም ጊዜ በላይ በእጅጉ እንሻለን።

በፓለቲካ አስተሳሰባችን እዚህ ወይንም እዚያ ልንቆም እንችላለን። የአንደኛው ወይም የሌላኛው አስተሳሰብ አራማጅ ልንሆን አንችላለን። የ"እኔ ሃሳብ የተሻለ ነው፣ የበለጠ ይጠቅማል" ብለንም ልንፎካከርም እንችላለን። መሠረታዊው ጉዳይ ሁላችንም ለዚህች ሀገር ጥቅምና የተሻለ ነገር ፍለጋ የተሰማራን መሆናችን ነው፤ እርግጠኝነትና ልባዊነት የሚያስፈልገው እዚህ ላይ ነው።

ብዕራችሁ የተባ፣ አዕምሯችሁ የሰላ እንዲሁም ተሳትፏችሁ ደግሞ የነቃ መሆን ዘመኑ ራሱ ይጠይቃል። መንግስት ይሄን ድባብ እንዲፈጠር አቅሙ የፈቀደውን ጠጠር መወርወር እንጂ የዜጎች ባላጋራና የዲሞክራሲ ስርዓት ደንቀራ መሆን አይገባውም። ይሄ ያፈጀበት አካሄድ ነው።

በምንገነባው ስርዓት በዴሞክራሲ ግንባታ እና በሰብዓዊ መብት አያያዝ ያለፉትን ስርዓቶች መርገምና መውቀሳችን ሳያንስ በዚህ ዘመንም አሳፋሪና አሳዛኝ ድርጊቶች ተፈፅሟዋል። ብዙ ዋጋም አስከፍለውናል።

ከዚህ በኋላ ፀረ-ዴሞክራሲ በቃ ብለናል፤ እያንዳንዱን ድርጊታችንና ስራችንን በንቃት ተከታተሉ። አካሄዳችንና ሁኔታችን ከዴሞክራሲ ያፈነገጠና የዜጎችን መብት የሚጋፋ ሆኖ በተገኘበት ጊዜ ሁሉ ልትታገሉን እና አደብ ልታስገዙን ይገባል።

በዚህ አያያዝ ኢትዮጵያውያን በነፃ አገራቸው፣ በነፃነት የሚያስቡባት፣ በነፃነት የሚፅፉባት፣ ያለ ገደብ የሚመረጡባትና የሚመርጡባት፣ የዴሞክራሲና የፍትህ ስርዓትን የሚመሩና የሚያስተባብሩ የጋራ ተቋማት የተገነቡባት፤ ዴሞክራሲያዊ አገር ባለቤት ይሆናሉ።

ይህ የህዝብ ጎርፍ፣ ሚሊዮኖች ያላንዳች ልዩነት በተባበረና ከፍ ባለ ድምፅ እየዘመሩለት ያለውን ኢትዮጵያን የዳበረና የተረጋጋ ዴሞክራሲ ባለቤት የሆነች አገር የማድረግ ጉዞ ነው።

ነገር ግን ዕዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው አንድ ታላቅ ቁም ነገር አለ። ዲሞክራሲ እንደፈለግን እንድንሮጥ እንደሚያስችለን፤ ሁሉ ልጓምንም ያበጃል። ልጓሙ የየግል ሩጫችንን በህግ ጥበቃ የተበጀላቸው የሌሎች የዜጎችን መብቶች እንዳይጋፉ ሲባል የተበጀ ነው። እናም የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ነፃነትንና ሃላፊነትን በሚዛኑ ያያዘ መሆን ይገባዋል።

ፍቅራችንና አብሮ የመኖር ዕሴታችን ዕንዲሁ በምስጋና ቀንና በሰላሙ ጊዜ ብቻ የምናሳያቸው ሳይሆኑ በችግርና በፈታኝ ወቅትም ቢሆን ፀንተው የሚቆዩ ሃብቶች ናቸው። በዚህ የአብሮነትና የአካታችነት ባህሪያችንን የሚሸረሽሩ አዝማሚያዎችን በጽናት ማውገዝ ይጠይቀናል።


የአማራ ክልል ህዝብ በአገራችን ቀደምት የገናናነት ታሪክ የበኩሉን ወሳኝ ሚና የተጫወተ ባለታሪክና ኩሩ ህዝብ ነው። አለመታደል ሆኖ ያ! የገናናነት አገራዊ ቁመና ተቀይሮ የከፋ ድህነትና ኋላቀርነት ቸነፈር ውስጥ ብዙ ዋጋ የከፈለ ነው። የአማራ ብሄር በታሪክ፣ በባህልና በቋንቋ እንዲሁም በሌሎች እሴቶች በአገር ግንባታ ሂደት ትልቅ ቦታ ያለው ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፉት ስርዓቶች ጥቂቶች ከሌሎች አካላት ጋር በጥቅም ተሳስረው በፈፀሙት ስህተት፤ በአማራው ላይ በተካሄደ የተሳሳተ አስተምህሮ ሰፊው የአማራ ህዝብ በሌሎች ህዝቦች በዳይ፣ ዕዳ ከፋይና የተለየ ተጠቃሚ መስሎ እንዲታይ አድርጎታል። በዚህ ብዙ መፈናቀል፤ ተጠርጣሪ እና ለሌሎች ችግሮች እንዲጋለጥ ሆኗል።

ከዚህ አኳያ የነበሩ ስህተቶችን በማረም የብሄራችንን እና የሃገራችንን ክብር ተመልሶ ገናናነታችንን ለማረጋገጥ መረባረብ ይገባናል። "ትልቅ ነበርን፤ ትልቅም እንሆናለን!" ይለዋል እንዲህ ነው።

ይህን ታላቅ ክልላዊና አገራዊ ራዕይ እውን ለማድረግ መሪ ድርጅቱ ብአዴን/ኢህአዴግ ላስመዘገባቸው ጅምር ስራዎች እንደሚመሰገን ሁሉ ላጠፋውና ላጎደለው ሃላፊነቱን ይወስዳል።

አሁን የተጀመረው የለውጥ ማዕበል ካለፈው ጉድለት ተምሮ በፅናት መጓዝን ይጠይቃል። ይህን የለውጥ ማዕበል በሙሉ ልብ ተቀብሎ ድርሻን መወጣት የግድ ይላል። ከዚህ ውጭ በእኔ አውቅልሃለሁ ፈሊጥ መንታ መንገድ መወጠን አይቻልም። መፍትሄው የህዝብን የለውጥ ፍላጎት አድምጦ ከእሱ ጋር በመሰለፍ ለውጡን በትክክለኛ አቅጣጫ መምራት ብቻ ነው።



ኢትዮጵያ አንዳንዶቻችን የቅንጦት ህይወት የምንገፋባት እና እንዳሻችን የምንፈነጭባት፤ ሌሎቻችን ደግሞ ባይተዋር የምንሆንባት ሀገር መሆን የለባትም። እናም በእናት አገርና በጋራ ጎጆችን በእኩልንትና በፍቅር እንኖራለን።

አገራችን በተያያዘችው የለውጥ መንፈስ አስቀድመው ለተፈፀሙ እኩይ ታሪኮች ዳግም እንዳይፈፀሙ ትምህርት ወስደንባቸው፤ አዲስ ታሪክ ለመስራት ደግሞ የተለኮሰውን መነሳሳት ሂደቱን በአግባቡ ልንመራውና ልንገራው ይገባል።

በቅርቡ በመዲናችን አዲሳ አበባ በንፁሃን ዜጎቻችን ላይ የደረሰው ጉዳት በአገራችን የሚደረገው የዴሞክራሲ ስርዓት ምንም እንኳን በወሳኝነት በፍጥነት መጓዝ እንደሚቻል ከወዲሁ አፋችን ሞልተን ለመናገር ቢያስችለንም ሂደቱ የአልጋ ባልጋ ጉዞ እንደማይሆን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ክስተት ነው።

በዚህ አጋጣሚ እኔና ባልደረቦቼ ክልላችንና ኢትዮጵያን የተረጋጋና የዳበረ ዴሞክራሲ ባለቤት የማድረግ የቤት ስራን ዳር ለማድረስ ከህዝባችን ጋር በመሆን በፅናት እንደምንዘልቅ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

በታሪካችን አንዳችን በሌላችን ላይ ተነስተናል። ሲከፍም ቃታ ስበን አንዳችን የሌላችንን አካል አቁስለናል። አልያም አጉድለናል። ምንም እንኳ ትናንት የተከሰቱ መጥፎ ታሪኮችን መዘንጋት ሰዋዊው የማስታወስ ችሎታችን የማይፈቅድልን ቢሆንም ለወደፊት የጋራ ጥቅምና ጉዞ ሲባል ሆን ተብሎ እኩይ ትዝታዎችን መቀየር በእጅጉ ያስፈልጋል።

እናም እንደዚህ ዓይነቱን ቅስቀሳና ውትወታ የሚያስተላልፉት ሃይሎች ጆሮ ዳባ ልበስ ልንላቸው ይገባል። አማራ የሚታወቅበት መለያ ባህሪው አካታችነቱና አቃፊነቱ ነው። አማራ የሚታወቅበትን እሴቶችን ጠብቆ መቀጠል የሚገባው ሲሆን፤ ተናጥል ችግሮች እንኳ ቢያጋጥሙ ህዝብን እና ግለሰብን ለይቶ እንዲታረም እና እንዲስተካከል ማድረግ እንደሚገባ፤ ከዚህ ውጭ የጥላቻ፣ የዘረኝነት፣ የበቀል እና የጎጠኝነት አረሞችን በማስወገድ ብቻ ሳይሆን ይህው ለትውልድ እንዳይተላለፍ ተግተን መስራት ይኖርብናል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ከይቅር ባይነት በላይ የምናከብረውና ዋጋ የምንሰጠው ነገር የለም። “ ይቅርታ” በልባችንም በመሐላችንም ትልቅ ቦታ አለው። ዛሬም ይህንን ቦታውን ልናሰፋ መሐላችንም ይቅርታ እርስት እንዲሆን እንውደድ። ይቅር አንባባል። ለየአካባቢው የሚታየውን ግጭትና መቃቃር ከመሠረቱ አክስመን በይቅርታችን እንደይመለስ አድርገን እንጠበው።

ኢትዮጵያውያን ነንና ይሄ አያቅተንም። በትንሹም ሆነ በትልቁ ሆድ መባባስ ቀርቶ አንዳችን ለሌሎችን የፍቅር ማዕድና አውድ እንሁን።

በሚሊዮኖች ተደግፎ የተቀጣጠለው ለውጥ ወደ ኋላ መመለስ ቀርቶ ማዝገምን አይታገስም። መፍትሄው በህዝብ ባለቤትነት እና በወጣቱ መሪነት በፍጥነት መጓዝ ነው። ካሁን በኋላ ሃገራችን ለሁሉም በእኩል የተመቸች፤ ዜጎቿ እኩል የሚደመጡባት፤ እኩል የሚሳተፉባት የጋራ ማዕዳችን ሆና ትቀጥላለች። ለዚህ እውን መሆን በፅናት መታገል ይኖርብናል።

ከዚህ አኳያ የስራ ባልደረቦቼ እና እኔ ቴዎድሮስና ገብርዬ ሆነን ተጋግዘን፤ አለቃ እና ምንዝር ሳንሆን፤ የአንድ አላማ ተሰላፊዎች በመሆን ህዝባችንን የሰላም፤ የዴሞክራሲ እና የልማት ፍላጎት ዳር እናደርሳለን።

በዚህ አጋጣሚ አበክሬ ላነሳ የሚገባ አንድ ቁም ነገር አለ። በኛ በአመራሮቹ በኩል፤ ህዝቡን በሚፈለገው ደረጃ ያለማዳመጥ፤ ያለማቀፍ፤ ያለማቅረብ፤ እና ለያይቶ ማየት ችግር አለ። እንዲሁም በምሁራኑ እና በወጣቱ እንዲሁም ባለሃብቱ የዳር ተመልካች የመሆን እና በራስ አገር ላይ ባይትርነቱ ተስተውሏል።

ክልላችንም ሆነ ሃገራችን ወደ ፊት ሊገሰግሱ የሚችሉት እና በለውጡ ዘልቀው ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጡት እኛ አመራሮቹ ችግራችንን ቀርፈን አቃፊና ደጋፊ ስንሆን ወጣቱ፤ ምሁሩ እና ባለሃብቱ ደግሞ ባይተዋርነቱን ትቶ የሃገሬ እና የክልሌ ጉዳይ ያገባኛል ደግሞም አመራሮቹ፤ የኔ ክፋይ ናቸው ብሎ አብሮ ሲሳተፍ እና ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲገባ ብቻ ነው።

እርግጠኛ ሆኜ የምነግራችሁ ከእንግዲህ እንደማንሳሳት ሳይሆን እንደምናደምጣችሁ፣ እንደከዚህ ቀደሙ ዘግይተን ሳይሆን ፈጥነን እንደምንመልስላችሁ እና በዚያው ፍጥነት እንደምንስተካከል ነው። ምስጋናችሁን ብቻ ሳይሆን ተግሳፃችሁን ከልብ ሰምተን ፈጥነን ለመታረም ዝግጁ መሆናችንን በልበ ሙሉነት አረጋግጥላችኋለሁ።

በተቻለን መጠን ባለን አቅም ሁሉ በህዝባዊነት እንደምናገለግላችሁ፣ ደከመን ሠለቸን ሳንል ሃላፊነታችንን ለመወጣት ጥረት እንደምናደርግ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

"የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ!" በሚል ዕሴት ታንፆ ለቃሉና ለማዕተቡ ታማኝና ሟች ከሆነ የታላቁ ህዝባችን ክፋዮች ነንና ይህንን ቃል እንጠብቃለን።

በዚህ አጋጣሚ ብአዴን በአማራው ስም በውጭ አገር የተደራጁና ለሱ የሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅች፣የተለያዩ ማህበራዊ የሚዲያ ተቋማት በሰላም ለመንቀሳቀስ እስከወሰኑ ድረስ ወደ ክልላችን መጥተው እንዲቀሳቀሱ ጥሪ እያስተላለፈ እኛም ከግማሽ መንገድ ድረስ ተጉዞ ለህዝባችን ጥቅም መከበር አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆናችንን አረጋግጣለሁ።■



አቶ ገዱ አንዳርጋቸው
በባህር ዳር በተደረገው የድጋፍ ሰልፍ

## አቶ ገዱ አንዳርጋቸው

## በባህር ዳር በተደረገው የድጋፍ ሰልፍ

ከሁሉ በማስቀደም በሚያለያዩንን ጉዳዮች ላይ ጊዜያችንን ማባከኑን ትተን አንድ በሚያደርጉን ጉዳዮች ለመተሳሰር በመፈለግ ቃል ወደምንገባበት የ“መደመር” ቀን ሁላችንም እንኳን አደረሰን!

ሃገራችን ከአመታት የሰላም እጦት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወጥታ አንፃራዊ ሰላም የሰፈነባት ናህዝቦቿ አንድ መሆን የጀመሩበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። የጥይትድምፅና ለቅሶ ያደነቁራቸው የነበሩ ከተሞቻችን ሰላምንና ፍቅርን ከፍ አድርገው መዘመር ጀምረዋል።

ልጅ እንደወጣ ይቀራል ብለው ሰቀቀን ውስጥ ወድቀው የነበሩ የእናት አንጀቶች በሰላም ማረፍ ጀምረዋል። ይህ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን የትናንቱ ገናና ታሪካችንና የነገው ታላቅ ተስፋችን ማስተሳሰሪያና ማረጋገጫ ማህተምነው።

የአማራ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር አንድ በመሆን በሀገራችን ጠንካራ መንግስት እንዲመሰረት፣ ታሪክ እንዳይበላሽና ነፃነት እንዳይገፈፍ ጥንትም ጀምሮ የሰራና የታገለ ጀግና እና ባለ ታሪክ ህዝብነው። የእንግሊዝ ወራሪ ኃይልን ፊት ለፊት ከመጋፈጥ እስከ አድዋ ድል፣ ከኢትዩጵያ አንድነት ምስረታ እሰከ አፍሪካ ዉህደት ጥሪና ገቢር ድርስና ከዚህም በኋላ ሃገራዊና አህጉራዊም ገድል እየፈፀመ የመጣ ህዝብ ነው።

የኢትዮጵያ ታሪክና ትውፊት ከትውልድ ትውልድ ሳይዛባ እንዲተላለፍ ከመፃፍ ከትቶ እስከ ማስቀመጥ የዘለ ቀሃገራዊ ውለታ ያለው ህዝብ፣ ለተራበ ፈትፍቶ አጉራሽ፣ ለተጠማ ቀድቶ የማይበቃው፣ ለወደደው ማርና ለጠላውም ኮሶነው።

ዛሬ በሀገራችን እየታየ ያለው የለውጥ ተሰፋ ደርዝ ያለው እንዲሆን የአማራ ህዝብ ተደራጅቶም ሆነ በተናጠል የሰራው ታሪክ ዘመን የማይሽረው ነው ብለን ብንናገር መታበይ አይሆንም። ሁላችሁንም የዚህ አንጸባራቂ ታሪክ ባለቤቶች ናችሁና እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ደስ አለን ስላችሁ በኩራት ነው።

ሃገራችን ከወደቀችበት እንደገና መነሳት ጀመረች እንጅ ገና በቅጡ መራመድ አልተቻላትም። አሁን ያሳየነውን አንድነትና ፍቅር በማይናወጥ መሰረት ላይ አንፀንየኔን፣ የእናንተን፣ የልጆቻችንንና የልጅልጆቻችንን እድል ተሰፋ እንዲበቅልበት ማድረግ ካልቻልን በዚህ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ በአጋጣሚ መገኘታችን ትርጉም የለውም። በስራችን ውጤት ዛሬ እንዲህ አምሮብንና ተውበን ብንታይም ልንሻገራቸው የሚገባ በርካታ ወንዞችና ሰበርባራ መንገዶች ከፊት ለፊታችን ይጠብቁናል። እንደጀመርነው ሁሉንም እናልፋቸዋለን። ግን ስንቅያስፈልገናል። ስንቁም ፍቅር፣ አንድነትና ተሰፋ ነው። አንድስንሆን የማይደፈሩ መስለው ይታዩ

የነበሩ ተራሮችን መናድ እንደምንችል ተምረናል። ስንደመር ብረትን ማቅለጥ እንደምንችል አይተናል። ስንፋቀር በሃገራችን የይቅርታና የምህረት ዝናብ እንደሚዘንብ ተገንዝበናል።

ዛሬ ሃገራችን ደስታና ፍቅር ብቻ የሚታይበት ሃገር አይደለችም። የኛ አንድ መሆን የእግር እሳት የሆነባቸው ያልታደሰውና የአሮጌው ዘመን ቁማርተኞች ከእግር እግራችን ስር እየተከተሉ መንገዳችንን በስጋት ድርሲ ያሰናከሉት ሲሞክሩ እየታዩ ነው። ሰላም የዋለው ሃገር ሰላም እንዳያድር፣ ለሰላም የተዘረጉ እጆች ሳይጨባበጡ እንዲቆረጡ ስራ ውለቴ ብለው የሚደክሙ ሽንፈትን ያልተቀበሉ ደካሞች ከዙሪያችን አልጠፋም። ድል መንሻው ዘዴ የታወቀና የተለየ ነው። አንድ መሆን፤ መደመር።ተለያይተን ሞክረነዋል አልተሳካልንም። ተነቃቅፈንና ተጠላልፈን አይተነዋል፤ የጅብ እራት ነው የሆን። እናም አንድነትን በጥብቅ እንሻለን። አንድነት የሚጀምረው ከቤት ነው። የአማራ ህዝብ ራሱ አንድ ሳይሆን ኢትዩጵያን ያህል ትልቅ ሃገር አንድ ለማድረግ አይቻለውም።

ከደጃችን ያለውን ቆሻሻ ሳናፀዳ ንፁህና የፀዳ ችሃገር መፍጠር ያዳግተናል። ረጅሙን የፍቅርና የአንድነት ጉዞ ከአጠገባችን ካሉ ቤተሰቦቻችን ጋር እጅ ለእጅ በመያያዝና በመተሳሰብ እንጀምረው።

ለክልላችን ወጣቶች

የክልላችን ህዝብ አፍላጉልበትን ከእውቀትና ከአስተዋይነት ጋር የተላበሰ ቆፍጣና ወጣት ይፈልጋል። እርምጃችሁ ሁሉ በማስተዋልና በጥበብ እንዲሆን፣ ስሜትንትታችሁ ምክንያታዊነትን፣ ጥላቻን ትታችሁ ፍቅርን፣ መገፋፋትን ትታችሁ አንተ ትብስ አንተ ትብስ መባባልን ሂወታችሁ በማድረግ በክልላችሁ የተጀመረው አንድነትና ተሰፋ እንዳይጨናገፍ ትታደጉት ዘንድ ጥሪ አቀርብላችኋለሁ። አሁን አንገት የምንደፋበትና ሙሾ እምናዎርድበት ወቅት አይደለም። ያለፈውን ረስተን በአዲስ ተስፋና ጥንካሬ ወደፊት እንራመድ።

ለሀይማኖት አባቶች

በሀገራችን ወንድማማችነትና እህትማማችነት መሰረቱ ሰፍቶ ታላቅ ታናሹን በተለመደው ኢትዩጵያዊ ባህል እንዲያከብርና ሰላም በሀገራችን እንዲበዛ ተግታችሁ ታስተምሩን ዘንድ እንደልጅነቴ በክብር እጠይቃችኃለሁ።

ለጥበብ ሰዎች

ትናንት ለሰላምና ለሰው ልጅ ክብር ያልተመለሰው ብዕራችሁ ዛሬም በምድራችን ፍቅርና መተሳሰብ እንዲሰፍን፣ ዲሞክራሲ እንዲስፋፋ፣ የተተባተበው እንዲፍታታ፣ የደበዘዘው እንዲተባ፣ የአማራ ህዝብ ታሪክ እንዳይዛባና እንዳይጠፋ አቅማችሁና የሞያ ደረጃችሁ በሚፈቅደው መጠን ሁሉ ከጐናችን ቁማችሁ እንድንተጋገዝና እንድንደመር ጥሪ አቀርብላችኋለሁ።

ለተፎካካሪ ፖርቲዎች

በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የአማራን ህዝብ በልማትና በዲሞክራሲ ተጠቃሚ እና ደርጋለን የሚል ሀሳብ ይዛችሁ የምትሰሩ ተፎካካሪ ፖርቲዎች እንዳላችሁ እናውቃለን።

አላማችሁና ፍላጐታችሁ የአማራን ህዝብ መጥቀም እስከሆነ ድረስ በፍቅር አይን እንመለከታችኃለን። ከፊታችን ያሉ ትልልቅ ችግሮችን ተራርቀን በመቆምልና ሽንፋቸው እንደማንችል ተገንዝባችሁ ከሀገርውጪ ያላችሁተመልሳችሁ፣ ኢትዩጵያ ውስጥ ያላችሁም ተቀራርበን አንድ በሚያደርጉን ነገሮች ላይ ተመስርተን አብረን እንስራ።

አንድ የሚያደርጉን ነገሮች ሁል ቆመሳፍርት የላቸውምና በሚያለያዩን ጥቃቅን ነገሮች ጊዜ ሳንጨርስ በጊዜ ወደቤታችን እንሰብሰብ።

ለአጐራባች ክልል ህዝቦችና ድርጅቶች

ዘመኑ አለም አንድ እየሆነ ያለበት ነው። አንዳችን የጐደለንን ሌላችን ሞልተን፣ የአንዱ ቤት የሌላውም ጭምር ይሆን ዘንድ ማንነታችን ጠብቀንና አክብረን በመካከላችን በማይገባ ያጠርነውን አጥር በጊዜ አፍርሠን በጋራና በመተባበር በመስራት አንዲት ጠንካራ ኢትዩጵያን ለመገንባት እንረባረብ።



ለክልላችንና ለፌዴራል መንግስት የፀጥታ አባላት ለክልላችንና ለመላ ኢትዩጵያ ሰላምና አንድነት እየከፈላችሁት ያላችሁትን ዋጋ አሳምሬ እገነዘባለሁ። ሀገራችን ሰላሟ የተጠበቀና እኩልነት የተረጋገጠባት ሆና እስክትዘልቅ ክንዳችሁ ሳይዝል፣ ነፃና ገለልተኛ ሆናችሁ የሰላም ምልክትነታችሁን መሰረት እንድታስይዙት አሳስባችኋለሁ። ኢትዩጵያ ንፁህ ደም ሳይሆን ፍቅር የሚፈስባት፣ በስጋት ሳይሆን በራስ መተማመን የተሞሉ ልጆች ያሏት ሃገር ትሆን ዘንድ የጀመራችሁትን ጀግንነት አበርትታችሁ እንድትቀጥሉ ጥሪ ቀርቦላችኋል።

ለሚዲያ ባለሞየወችና ጦማሪያን

በሃገራችን እየታየ ያለው ተስፋ ፍሬ ያፈራ ዘንድ እውነቱን ለህዝቡ አሳዉቁ። ከመላው ህዝባችን የምንደብቀው ጉዳይ የለንም። ስኬታችንም ሆነው ድቀታችን በልክ በልኩ እየተቆጠ ለህዝብ ጆሮ ይደርስ ዘንድ ሙያችሁ የሚጠይቀውን ዲስፕሊን ጠብቃችሁ ስሩ። ማዛባት ሁላችንንም ያጠፋናልና አሁን እንደጀመራችሁት ጣፋጭ ስኬትን ከመራራ እውነት ጋር አጣጥማችሁ ተራመዱ።

መጪው ጊዜ የአማራ ህዝብ የሚሰደድበት፣ የሚሸማቀቅበት፣ አንገት የሚደፋበት ሳይሆን በኩራት ቀና ብሎ የሚሄድበትና ከቁዘማ የሚላቀቅበት ነው። ከእንግዲህ ሆድ ሊብሰን አይገባም። ከእንግዲህ የትናነቱን እያነሳን መብሰልሰል ሳይሆን አንገታችንን ቀና አድረገን በተስፋ ወደፊት መራመድ ነው መለያችን። ሁላችንም ለዚህ እውን መሆን ተቀራርበንና ተደምረን እንስራ።